ILAP
IMMIGRANT LEGAL ADVOCACY PROJECT

# የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የመኖርያ ጥበቃ (ቲ-ፒ-ኤስ- TPS)

የአሜሪካ መንግስት፤ ከጥቅምት (October) 20 ቀን 2022 ጀምሮ በአሜሪካን አገር መኖር ለጀመሩ ኢትዮጵያውያን ግዜያዊ የመኖርያ ጥበቃ **(TPS, Temporary Protected Status)** በመስጠት ላይ ይገኛል።

---

## ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ምን ማለት ነው?

ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ማለት ሰዎች **ከአገር እንዳይባረሩ ጥበቃ የሚያደርግ፤ ህጋዊ የመኖርና የስራ መስራት ፈቃድ ((Employment Authorization Card)** የሚሰጥ ነው። ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ጊዜያዊ ነው። በወቅቱ የተደረገው የኢትዮጵያ ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ከ ታሕሳስ ((December) 12 ቀን 2022 እስከ ሰኔ (June)12 ቀን 2024 ድረስ ለ18 ወራት የሚያገለግል ነው። የሚያከትምበት ቀን ከመድረሱ በፊት፤ የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ የሰጠውን ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ለማራዘም ወይም ለማቋረጥ ውሳኔ ያደርጋል።

---

## የኢትዮጵያን ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ለማግኘት ብቁ ነኝን?

ለኢትዮጵያን ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ብቁ የሚሆኑት:

**የተወሰኑ ዓይነት ወንጀሎችን ከፈጸሙና በአንዳንድ ሌሎች ምክንያቶች ለቲ-ፒ-ኤስ (TPS)* ብቁ ላይሆኑ ይችላሉ።*

- የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆኑ እና
- አሜሪካን አገር ውስጥ ከጥቅምት (**October**) **20 ቀን 2022** ወይም ከዛ በፊት መኖር ከጀመሩ ነው።

### የኢትዮጵያን ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ለማግኘት ሲያመለክቱ አንዳንድ ዶኩመንቶችን ማሰባሰብ ያስፈልጎታል፡

- የኢትዮጵያ ፓስፖርት፣ የተወለዱበት የምስክር ወረቀት ወይም የአገር መታወቅያ ወረቀት
- ወደ አሜሪካን አገር የገቡበት ማስረጃ ለምሳሌ ቪዛ፣ የፓስፖርት ቴምበር፤ **አይ-94** (I-94) ወይም ኤን-ቲ-ኤ (NTA, Notice to Appear)
- ከጥቅምት (October) 20 ቀን 2022 ጀምሮ አሜሪካን አገር ውስጥ እንዳሉ የሚያሳዩ እንደ የሃኪም ወረቀቶች፣ የቤት ኪራይ ውሎች፣ የ ደሞዝ ክፍያ ወረቀት ወይም የትምህርት ቤት መዝገቦች የመሳሰሉ
- በአሜሪካን አገርም ሆነ በማንኛውም ሌላ አገር ወንጀል ፈጽመው የታሰሩበት፣ የተወነጀሉበት ወይም በወንጀል ፍርድ ቤት የታየ ጉዳዮን የሚያሳዩ ዶኩመንቶች
- ቀደም ሲሉ የሞሏቸው የኢሚግሬሽን ማመልከቻዎች ካሉ የእነሱን ቅጂ

## የኢትዮጵያን ቲ-ፒ-ኤስ (TPS) ለማግኘት እንዴት ነው የማመለከተው?

- ሜይን (Maine) ውስጥ የሚኖሩ ከሆነና የኢትዮጵያ ቲ-ፒ-ኤስን (TPS) ለማግኘት ማመልከት ከፈለጉ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ዶኩመንቶች ያሰባብስቡና) ከስደተኞች ህጋዊ ጠበቃዎች ፕሮጄክት ከኢላፕ (ILAP) ጋር ለመገናኘት በኦንላይን ወደ **www.ilapmaine.org/get-legal-helpl** በመግባት ቀጠሮ እንዴት እንደሚወሰድ መረጃ ያግኙ።

ይህ መረጃ በ https://ilapmaine.org/ ይገኛል። ይህ ጽሁፍ የተከለሰው መስከረም (December) 12 ቀን 2022 ነው።

IMMIGRANT LEGAL ADVOCACY PROJECT

- ከሰኔ (June) 12 ቀን 2024 በፊት ማመልከቻዎን ያስገቡ። ኢላፕ (ILAP) በተቻለ መጠን ተቀላጥፎ ማመልከት የተሻለ መሆኑን አስተያየቱን ይሰጣል።
- አንዳንድ ሰዎች በኢሚግሬሽን ጉዳዮ የሚረዱ መስለው ከቀረብዎት በኋላ ገንዘቦን ብቻ ለመውሰድ የሚፈልጉ ስላሉ ከእንዲህ ዓይነቶቹ አጭበርባሪዎች ይጠንቀቁ። ከእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች እንዴት ራሶን መጠበቅ እንደሚችሉ ወደ https://ilapmaine.org/protect. ይግቡና ትምህርት ይቅሰሙ።